# ለላቀ አንድነት…

**ዘአማን በላይ** 05-27-18

27ኛውን የግንቦት 20 የድል በዓልን በሀገር አቀፍ ደረጃ ነገ እናከብራለን። ዕለቱ “የላቀ ብሔራዊ መግባባትና ዴሞክራሲያዊ አንድነት ለላቀ አገራዊ ስኬት” በሚል መሪ ቃል ይከበራል። የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ውልደት፣ መሰረትና ብስራት የተሰማበት ይህ የድል በዓል፤ ከወዲሁ በመላ ሀገሪቱ መከበር ጀምሯል። እንዲሁም ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በሚገኙባቸው የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች፣ ሚሲዮኖችና የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ ማህበረሰቦች ውስጥ በተለያዩ ዝግጅቶች በመከበር ላይ ይገኛል።

ድሉ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብዝሃነትን ያከበረ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲገነባ በከፈሉት መስዕዋትነት የተገኘ ነው። ኢትዮጵያችን እንደ አዲስ እንድትገነባ መሰረት የጣለና የሀገሪቱ ዜጎች ማንነታቸው ተከብሮ በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ለመገንባት ህገ መንግስታዊ ዋስትና ያገኙበት ዕለትም ነው።

ርግጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በህገ መንግስታቸው የጋራ ጉዳዮቻቸውን በጋራ ለማስተዳደር፣ የፌዴራል መንግስት መስተዳድርን ለማቋቋም፣ እያንዳንዳቸው ራሳቸውን የማስተዳደር መብታቸውን ተግባራዊ ለማድረግ በሰፈሩበት መልክዓ ምድር ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበት መንግስታዊ ተቋማትን ለማቋቋም እንዲሁም በክልልና በፌዴራል መስተዳድሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና ማግኘት ችለዋል። ይህም የሀገራችን ህዝቦች በውስጣቸው ዴሞክራሲያዊ አንድነትን ማጎልበት የሚችሉበትን ዋስትናን የሰጠ ነው።

ባለፉት ስርዓቶች ገቢራዊ ሆኖ የነበረው አሃዳዊ ስርዓት በኢትዮጵያ የህዝቦች መካከል ቅራኔንና መካረርን እንዲሁም የመበታተን አደጋን ፈጥሮ እንደነበር ግልፅ ነው። ላለፉት 27 ዓመታት ዕውን የሆነው የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ስርዓት ግን በመፈቃቀድ፣ በየደረጃው ገቢራዊ በሚሆን እኩል ተጠቃሚነትና በሰፊ የክልሎች ስልጣን በመመስረቱ ለልማትና ለዴሞክሲያዊ አንድነት እንዲሁም ለሰላም ዋስትናን ፈጥሯል።

አዎ! ለ27ኛ ጊዜ የምናከብረው የግንቦት 20 የድል በዓል የሀገሪቱ የወደፊት ተስፋ እንደገና እንዲያንሰራራ በማድረግ እንደ ሀገር ለመቀጠል ተደቅኖ የነበረውን ስጋትና ሁኔታ መቀየር ችሏል። ሁሉንም ህዝቦች የሚያስተባብር አዲስ የፖለቲካ ስርዓት በመገንባት የሀገሪቱን ህልውና ያስቀጠለም ጭምር ነው።

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዘላቂ ሰላም፣ ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት እንዲሁም ዋስትና ያለው ዴሞክራሲን ለማረጋገጥ መደላድል የፈጠረና ያስቻለም ነው። በዚህም ሳቢያ በሀገሪቱ ውስጥ ብዝሃነት የተቀበለና ያከበረ አዲስ ህገ መንግስታዊ ፌዴራላዊ ስርዓት መፍጠር ተችሏል።

የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በሀገራችን ዘላቂ ሰላምና ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን እንዲሁም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገታችን እንዲፋጠን ለማድረግ በነፃ ፍላጎታቸው በህግ የበላይነትና በራሳቸው ፈቃድ ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ የመገንባት ዓላማን የሰነቀ ነው።

የሀገራችን ህዝቦች መጪው የጋራ ዕድላቸው መመስረት ያለበት ከታሪካቸው የወረሱትን የተዛባ ግንኙነት በማረምና የጋራ ጥቅማቸውን በማሳደግ ላይ እንዲመሰረት ፈቅደውና አምነው ገቢራዊ ባደረጉት ህገ መንግስታቸው ቃል

ገብተዋል። ይህም በተደጋጋፊነት፣ በፍትሐዊነትና ፈጣን ልማት ለማሳደግ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መገንባት አስፈላጊነትን የያዘና በአዲስ መንፈስ ለአዲስ የሀገር ግንባታ ፈር የቀደደ ነው።

አዲሲቷ ኢትዮጵያ የየራሳቸው አኩሪ ባህል ያላቸው ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሀገር ናት። የየራሳቸው መልክዓ ምድር አሰፋፈር የነበራቸውና ያላቸው በተለያዩ መስኮችና የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረው አብረው የኖሩባትና የሚኖሩባት ሀገርም ናት። የዚህች ሀገር ህዝቦች በአንድነት ያፈሩት የጋራ ጥቅምና አመለካከት ያላቸውና ይህንንም ለማጎልበት ዕድል የተመቻቸላቸው ናቸው።

እነዚህን እውነታዎች በህገ መንግስታዊ ስርዓቱ ውስጥ ለመተግበር አንዱ የበላይ፣ ሌላኛው የበታች ሳይሆን በእኩልነትና በጋራ ተጠቃሚነት ስሜት እንዲጓዙ የሚያደርጋቸው ነው። ይህም የትኛውም ማህበረሰብ የራሱን ጉዳይ በሚመለከት የራስ አስተዳደር እንዲሁም የጋራ ጉዳዮችን በጋራ የማስተዳደር ኃላፊነትና ስልጣን እንዲኖራቸው አድርጓል። ባለፉት ዓመታት ዴሞክራሲያዊ አንድነት ለመፍጠር ህዝቦች የእኩልነት መብታቸው ህገ መንግስታዊ ዋስትና አግኝቷል።

በዚህም የእኩልነት ማረጋገጫ የሆኑት የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቋንቋዎች፣ ባህሎች፣ ታሪኮች...ወዘተ. ያለ አንዳች አድልኦ እንዲከበሩ ተደርጓል። ዜጎች በፖለቲካውና በልማቱ ረገድ እኩል የመሳተፍ መብት አግኝተዋል። በውጤታቸው መሰረትም አቅም በፈቀደ መሰረት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል። ይህም በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ አንድነትን በመፍጠር በሀገር ግንባታ ሂደቱ ላይ ጉልህ ሚና ሊጫወት ችሏል የሚል እምነት አለኝ።

ያም ሆኖ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የሀገር ግንባታ ሂደት እንከን አልባ ነበር የሚባል አይደለም። በተለይ የህብረተሰቡን ፍትሐዊ ተጠቃሚነት በሚገባው ደረጃ ካለማረጋገጥ ጋር ተያይዞ የመልካም አስተዳደር ችግሮች መፈጠራቸውና ይህም የስርዓቱ ባህሪ ወዳልሆነው ግጭት እንዳመራን የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። በብስራትና በስጋት መካከል እንድንሆንም አድርጎን ነበር።

በተለያዩ ወቅቶች የተፈጠሩት የአፈፃፀም ስህተቶች፣ ከስርዓቱ ውልደትና ዕድገት ጋር ተያይዘው የተከሰቱ ነባራዊ እውነታዎች፣ የአቅም ውስንነቶች፣ ኪራይ ሰብሳቢነትና ሙስና እንዲሁም የሃይማኖት አክራሪነት ብቅ ጥልቅ እያለ መከሰቱና ዴሞክራሲያዊ አንድነት በተገቢው ሁኔታ አለመስረፅ እንከኖች ወይም ተግዳሮቶች ነበሩ። እነዚህ ችግሮች በየጊዜው ስርዓቱን ዋጋ አስከፍለውታል። እንዲያውም ሀገራችን በመስቀለኛ መንገድ ላይ እንድትቆም አድርገዋት እንደነበር አይዘነጋም።

እነዚህ ችግሮች እኔን ጨምሮ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ‘በብስራተ አዲሲቷ ኢትዮጵያ የተገኙት ድሎች የኋሊት ይሄዱ ይሆን?’ የሚል ጥያቄ እንዲያነሳ አድርጎት ነበር። ዳሩ ግን ምስጋና መንግስትን ለሚመራው ኢህአዴግና የዜጎችን ተስፋ እያንሰራሩ፣ ክብርን እየመለሱና ጥቅምን እያረጋገጡ ላሉት የድርጅቱ ሊቀመንበር ዶክተር አብይ አህመድ ይሁንና ዛሬ ተስፋን ሰንቀናል። ከፊታችን በክብር ላይ ክብር ስንጎናፀፍ ይታየናል። “ትንቢት ይቀድም ለነገር” እንዲል መፅሐፉ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከአንድ ወር እልፍ ባለ ጊዜ ውስጥ ብቻ አንገታችንን ቀና አድርገን በአዲስ ኢትዮጵያዊ መንፈስ ወደፊት አሻግረን እንድናይ አድርገውናል። የአዲሲቷን ኢትዮጵያ ወግ፣ በሀገራዊ መዝሙራችን ላይ ያለውን “የዜግነት ክብር” አግኝተን ታላቅ ሀገራዊ ማዕድን እየተቋደስን ነው። መዓዱ ህፃኑን፣ ወጣቱንና አዛውንቱን ሳይለይ ለመላው የሀገራችን ህዝብ ቀርቧል። ይህን ኢትዮጵያዊ ክብርን የሚያጎናፅፍ መዓድ ማስፋትና የእሳቤውን ደርዝ ጥልቀት በመጨመር ይበልጥ ተቋዳሽ መሆን ከሁሉም ዜጋ የሚጠበቅ ይመስለኛል።

ዛሬ በአዲስ ሁኔታ የግንቦት 20ን ድሎቹን ግለቱን ጠብቆ ወደፊት በማስቀጠል ከመልካም አስተዳደር ጋር የተያያዙ የአፈፃፀም ስህተቶችን ግልፅነት፣ ተጠያቂነትና አሳታፊነት ባለው አሰራር በመፍታት ህብረተሰቡን ከመንግስት ማግኘት የሚገባውን እርካታ ለማረጋገጥ መንግስት ጥረት እያደረገ ነው።

ኪራይ ሰብሳቢነትንና ሙስናን ለመከላከል አዲሱ የመንግስት አመራር አስተሳሰቡንና ተግባሩን “በቀይ መስመርነት” ፈርጆ ወደ ስራ ገብቷል። ይህ የመንግስት ቁርጠኛ አቋም ተፈላጊውን ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል ጥርጥር የለውም። የሃይማኖት አክራሪነት አስተሳሰቦችን በሀገር ግንባታ ስራ ላይ ሊያሳርፉ የሚችሉትን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመፍታት በህገ መንግስቱ ላይ የተቀመጡትን የሃይማኖት እኩልነትንና የእምነት ነፃነትን ይበልጥ በማረጋገጥ እንዲሁም የአክራሪነትን አደጋ በማመላከት እንደ ሀገር ለመቀጠልና የምንፈልግበት ግብ ለመድረስ እንድንችል መንግስት በበቂ ሁኔታ እየሰራ ነው።

ህገ መንግስታዊ ስርዓቱ ዴሞክራሲያዊ አንድነትን የሚያረጋግጥ ምቹ መደላድልን ፈጥሯል። ሆኖም በደንብ ታቅዶና በጥናት ላይ ተመስርቶ ተሰርቷል ለማለት የሚያስደፍር አይመስለኝም። እንዲያውም አንዳንድ ፅንፈኞች ከውስጥም ይሁን ከውጭ በመደራጀት ዴሞክራሲያዊ አንድነትን በሚያቀጭጭ መንገድ ሲሰሩ እንደነበር እናስታውሳለን። እነዚህ ሃይሎች የስርዓቱ መሰረት የሆነው ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነትን ለመድፈቅም ሰርተዋል። ያም ሆኖ መንግስት ኢትዮጵያዊነትንና ዴሞክራሲያዊ አንድነትን ብሎም ሀገራዊ መግባባትን ሊፈጥሩ በሚችሉ ጉዳዩች ላይ በመስራቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤት እያመጣ ነው።

ስርዓቱ ከፈጠረው ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት ጋር አብረው የተከሰቱ የተጠቃሚነት ጥያቄዎች መንግስትን በሰዓቱ ያነቁና ምላሽ እንዲሰጥባቸው ያደረጉ ናቸው። የማስፈፀም አቅምን ለማጎልበትም ስራንና ሰራተኛን በማገናኘት እንዲሁም ትክክለኛውን አሰራር በማመላከት አቅምን በተናጠልና በቡድን በማጠናከር ችግሩን ለመፍታት ተጨባጭ ርምጃዎች እየተወሰዱ ነው።

ርግጥ በአሁኑ ወቅት የኢፌዴሪ መንግስት የግንቦት 20 የድል ውጤት የሆነችው አዲሲቷ ኢትዮጵያ በሀገር ግንባታ ሂደቷ ላይ ያጋጠሟትን ተግዳሮቶችን በጥሞና በመመልከት፤ ችግሮቹ በዘላቂነት የሚፈቱበትን መሰረታዊ መፍትሔዎች አስቀምጧል። መፍትሔዎቹን ተንተርሶ ተጨባጭና የሚደነቁ ርምጃዎችን በውሰድ ለውጥም እያመጣ ነው። በተለይም ሀገራዊ መግባባትንና ዴሞክራሲያዊ አንድነትን በማጠናከር ረገድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለውጥ ማምጣት ችሏል። የለውጡ ጅምሩ “ይበል!” የሚያሰኝና ወደፊት ጠንካራ አንድነት ያሏቸው ህዝቦች ሀገርን እውን በማድረግ ኢትዮጵያዊ ራዕይን የሚያሳካ ነው።

ታዲያ ይህ የሀገር ግንባታ ተግባር በመንግስት ጥረት ብቻ እውን ሊሆን አይችልም። ተግባሩ የእያንዳንዱን ዜጋ ርብርብ የሚጠይቅ ነው። እናም ዜጎች ብስራተ—አዲሲቷ ኢትዮጵያን እውን ያደረገውን ግንቦት 20 ድል በዓልን በያሉበት ሲያከብሩ የመንግስትን የለውጥ ሂደት በመደገፍ በአንድነት መቆም ይኖርባቸዋል።